


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## ክርስቶስ እንደወደደን፥ እርስ በርሳችን እንዋደድ ይሆን?

### በቃል የሚጠና፡- 1ኛ ዮሐ. 2፥9-11

***"ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዳችሁ፥***
***እኔም የምወዳችሁ በመሆኔ***
***በጣም እንደምናፍቃችሁ***
***ምስክሬ እግዚአብሔር ነው።"***
***(ፊልጵ. 1፥8)***

**-1-**

**የክርስቶስ ፍቅር ምን ዓይነት ነው?**

ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን "ክርስቶስ በሚወደው ዓይነትና ልብ፥ እኔም እወዳችኋለሁ፤ ለዚህም ምስክሬ እግዚአብሔር ነው" ይላቸዋል። ***"ክርስቶስ እንደሚወዳችሁ እወዳችኋለሁ"*** ሲል፥ "ክርስቶስ ባለው ዓይነት ልብ እወዳችኋለሁ" ማለቱ ነው። ጳውሎስ በድፍረት "ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዳችሁ እወዳችኋለሁ" ሲል፥ አነጋገሩ ድፍረት ያለበት ነው ሳንል አንቀርም። ሌሎችን የሚወድበት የክርስቶስ ልብ ለመሆኑ ምን ዓይነት ነው? የክርስቶስ ልብ ፍጹም ለስላሳ፥ ወይንም ልዝብ የሆነ ነው። ለስላሳ ልብ ያለው ስንል፥ በርህራሄ የተሞላ ማለታችን ነው። ጳውሎስ ክርስቶስ እንደሚወዳችሁ እወዳችኋለሁ ሲል፥ የክርስቶስ ፍቅር ጥልቀቱና ስፋቱ ምን ያህል እንደሆነ፥ በርህራሄ የተሞላ መሆኑን ሳይረዳ፥ ዝም ብሎ ለመናገር ብቻ የተናገረው እንዳልሆነ እናውቃለን። የኢየሱስ ፍቅር፥ ራሱን ለሚወዳቸው አሳልፎ እስከመስጠት ደረጃ ድረስ እንደሆነ በደንብ ያውቃል። ኢየሱስ ለወዳጆቹ ያለው ፍቅር ምን ዓይነት እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ አለ። ***"ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም"*** አለ (ዮሐ. 15፥13)። ይሄ ፍጹም የሆነው ኢየሱስ፥ ተከታዮቹም የእርሱን ዓይነት ፍቅር እንዲኖራቸው ይፈልጋል። ***"እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት"*** ይላል (ዮሐ. 15፥12)። ትእዛዙ፥ "ከቻላችሁ፥ ከፈቀዳችሁ፥ ደስ ካላችሁ፥ ከተስማማችሁ ዉደዱ" በማለት ምርጫ የሚሰጥ ሳይሆን፥ የማያዛንፍ፥ ወይንም ምርጫ የማይሰጥ እንደሆነ እንገነዘባለን።

**-2-**

**ክርስቶስ የሰጠን ትዕዛዝ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ነው**

***"እኔ እንደወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ"*** ብሎ ጥብቅ የሆነ ትእዛዝ እንደሰጠን ስንረዳ፥ "እርሱ የወደደን እንዴት ነው?" ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ለዚህ ጥያቄ አችን ሐዋርያው ዮሐንስ ግልጽ የሆነ መልስ ይሰጠናል። ***"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና፤ በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል"*** ይላል (1 ዮሐ. 3፥16)። ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ሰዎችን "ክርስቶስ እንደ ወደዳችሁ እኔም እወዳችኋለሁ" ሲል ከመስመር የወጣ ንግግር መናገሩ እንዳልሆነ እናምናለን። ሌላውን መውደድ የምንችለው እውነተኛ ፍቅር የሆነውን አምላክ መውደድ ስንችል ብቻ ነው። ይሄ ፍቅር የሆነውን ጌታ ስንወደው፥ መልሶ የማይወድ አምላክ አይደለም።

***የሕይወት ምሳሌ፡-*** አንዲት የአራት ዓመት ልጅ አሻንጉሊቷን እቅፍ አድርጋ እየሳመች እናቷን፥ "እማዬ! አሻንጉሊቴ ምንም ያህል ብወዳት፥ ምንም ያህል አቅፌ ብስማት፥ መልሳ አታቅፈኝም፥ እንደምወዳት አትወደኝም" አለች። ለብዙዎቻችን የእግዚአብሔር ቅርበቱ አይታየንም። የምንወደውን ያህል የሚወደን መስሎ አይሰማንም። እግዚአብሔርን ድንቅ የሚያደርገው፥ እኛን ለመውደድ ችግር የሌለበት፥ ሌላው ቀርቶ ሳንወደውም እንኳን የሚወደን መሆኑ ነው። እኔና እናንተ ግን መጠየቅ ያለብን፥ "የምወደው ጌታ ይወደኛል ወይ?" ብለን ሳይሆን፥ "የሚወደኝን ጌታ እኔ እወደዋለሁ ወይ?" ብለን ነው። ሰውን እየጠላነው "እወድሃለሁ" ማለት እንችላለን። እግዚአብሔር ግን ሁሉን ስለሚያውቅ ሳንወደው "እወድሃለሁ" ብለን መዋሸት አንችልም።

***የሕይወት ምሳሌ፦*** ጌታውን እንዴት መውደድ እንደቻለ አንድ ክርስቲያን ተጠይቆ ሲመልስ እንዲህ አለ። "አንድ ቀን እንደ ተለመደው ወደ መደበኛው የዕለት ሥራዬ ስሄድ፥ ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን ***"የዮና ልጅ ሲሞን፥ ትወደኛለህ?"*** የሚለው ጥያቄ ወደ አዕምሮዬ መጥቶ በውስጤ ማሰላሰል ጀመርኩ። ጴጥሮስ "ጌታ ሆይ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ" እንዳለው እኔም ማለት ብችል ምን ያህል ደስ ባለኝ ነበር ብዬ አሰብኩ። በሙሉ ልቤ ጴጥሮስ እንዳለው ***"ጌታ ሆይ! እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ"*** ማለት ባለመቻሌ ልቤ በሀዘን ተሞላ። እንደ ጴጥሮስ ለማለት ከከበደብኝ ሌላ ቀለል የሚል ነገር አገኝ እንደሆነ በማለት ማሰብና ማሰላሰል ጀመርኩ። ወዲያው ሌላው ቢቀር ***"ጌታ ሆይ! እንደማልወድህ አንተ ታውቃለህ"*** ማለት ግን እንደማልችል ተረዳሁ። ጌታን በድፍረት ***"አልወድህም"*** ማለት አለመቻሌን ስረዳ፥ በጣም ተጽናናሁ። ከዚህ በኋላ በድፍረት ተሞልቼ ***"ጌታ ሆይ! ልወድህ እንደምፈልግ አንተ ታውቃለህ"*** አልኩት። ይህን ብዬ ወዲያው እርሱ ስለ እኔ ያለውን ታላቅ ፍቅር ማሰብ ጀመርኩ። በምድር ስላሳለፈው የመከራ፥ የስደት ሕይወት፥ በመስቀል ላይ ስለተሰቃየው ስቃይ ማሰላሰል ጀመርኩ። ወዲያው የማደርገውንና የምናገረውን ሳላውቅ፥ ወደ ሰማይ ቀና ብዬ ***"ጌታ ሆይ! እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ"*** አልኩት። በዚያኑ ጊዜ ምህረቱና ይቅርታው ልቤን ሞላው፤ ከምንጊዜውም የበለጠ ከጌታዬ ጋራ የተቀራረበ ሕይወት እንዳለኝ ተሰማኝ" አለ።

**-3-**

**ከዚህ ክፍል ውስጥ የምናገኘው ጠቃሚ ትምህርት**

### ሀ *ፍቅራችን ከልብ የወጣ ይሁን*

ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ሰዎች ***"ክርስቶስ በሚወደው ዓይነት ልብ፥ እኔም እወዳችኋለሁ"*** ሲላቸው ለማለት ያህል ብቻ ሳይሆን፥ ፍቅሩ ከልብ የወጣ ነው። ይህን ዓይነት ፍቅር ማግኘት የቻለው፥ የማፍቀር ኃይልንና ፈቃድን ከእግዚአብሔር ስላገኘ ብቻ ነው።

### ለ *ሌላውን ሰው የምናፈቅረው እኛን ሲመቸን ብቻ አይደለም*

እኔና እናንተ መኖር ሲደክመን፥ ኑሮ ሲሰለችን፥ በተደራራቢ መከራ ውስጥ ስናልፍ፥ በልዩ ልዩ ምክንያት ስሜታችን ሲጎዳ፥ ከምንጊዜውም የበለጠ የሚወደንን እንፈልጋለን እንጂ፥ እኛ ሌላውን የምንወድበት አቅምና ጉልበት ያለን መስሎ አይሰማንም። ይሁን እንጂ፥ በዚህ ጊዜ ነው የፍቅር እርምጃ መውሰድ ያለብን። ሌላውን ሰው የምንወደው፥ ሁኔታዎች ጥሩ ሲሆኑልን ብቻ ሳይሆን፥ ሁልጊዜ መውደድ እንዳለብን ማወቅ ይገባናል።

### ሐ *ሌላውን መውደድ የሚያስችለን፥ በውስጣችን ያለው የክርስቶስ ፍቅር ነው*

ለማይገባው ሰው ፍቅራችንን ለመስጠት ውስጣችን እምቢ ሲለን፥ ፍቅራችንን ምንም ሳናስቀር እንድንሰጥ የሚያስችለን፥ የእኛ ጥረት ሳይሆን፥ በውስጣችን ያለው የክርስቶስ ፍቅር ነው። እርሱ የፍቅር አምላክ ስለሆነ፥ ፍቅር የሚጀምረው በእግዚአብሔር ፍቅር ስንሞላ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር በሰው ሕይወት ውስጥ ሲፈስ፥ የሰውን ሕይወት ይለውጣል፤ የክርስትናን ባህሪ በውስጣችን ይቀርጻል።

### መ *እውነተኛ ፍቅር በልባችን የሚፈሰው በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ ነው*

አንዳንዶቻችን ልባችንን ለመንፈስ ቅዱስ ሳንከፍት የመንፈስ ፍሬ የሆነው ፍቅር በሕይወታችን እንዲኖር እንታገላለን። ጳውሎስ ***"በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም"*** ይላል (ሮሜ 5፥5)። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልባችን የሚያፈሰው ፍቅር ልዩ ነው። ያለእግዚአብሔር ፍቅር ማንም ሌላውን ማፍቀር አይችልም። ፍቅር ከአምላክ ስለሆነ፥ ፍቅርን የመስጠትም ሆነ የመቀበልን ችሎታ ለእኔና ለእናንተ ሰጥቶናል። የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ማለት፥ ፍቅሩን ማስተላለፍ እንድንችል፥ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ይኖራል ማለት ነው። ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ምዕመናን ***"ክርስቶስ በሚወደው ዓይነት ልብ፥ እኔም እወዳችኋለሁ"*** ማለት የቻለው በዚህ ምክንያት ነው።




**የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፥ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።**

**(ኤፌሶን 6፥17)**




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

1. ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን እንደሚወድ ምስክር የጠራው ማንን ነው?

2. ጳውሎስ "ክርስቶስ እንደሚወዳችሁ እወዳችኋለሁ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

3. ኢየሱስ ለወዳጆቹ ስላለው ፍቅር ምን አለ? (የዮሐ. 15፥13)

4. ሐዋርያው ዮሐንስስ ስለ ክርስቶስ ፍቅር ምን አለ? (1 ዮሐ. 3፥16)

5. ኢየሱስ ትዕዛዜ ምንድነች አለ? (ዮሐ. 15፥12)

6. ሌላውን ሰው መውደድ የምንችለው መቼ ነው?

7. ሰውን እየጠላነው "እወድሃለሁ" ማለት እንችላለን። እግዚአብሔር ግን ማለት የማንችልበት ምክንያቱ ምን ድነው?

8. ለማይገባው ሰው ፍቅራችንን ለመስጠት ውስጣችን እምቢ ሲለን፥ ምንም ሳናስቀር እንድንሰጥ የሚያስችለን ምንድነው?

9. ፍቅርን እንዴት ማግኘት እንችላለን? (ሮሜ 5፥5)

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ...

1. ሌላውን መውደድ የራስ የሆነውን መተውን ይጠይቃል። ይህን ዓይነት የፍቅር ልምምድ፥ ሌላውን በመውደድህ/በመውደድሽ ምክንያት መስዋዕት የከፈልክበት/የከፈልሽበት ልምምድ አለህ/አለሽ?

2. "መውደድ አልችልም" የምትላቸው/የምትያቸው ሰዎች እነማን ናቸው?

3. በጥላቻ ተሞልተህ/ተሞልተሽ ክርስቲያን መሆን ስለማትችል/ስለማትችዪ፥ ምን ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ ተዘጋጅተሃል/ተዘጋጅተሻል?


❹

4. ጌታን እወዳለሁ፥ አንዳንድ ሰዎችን ግን መውደድ አልች ልም ማለት እንችላለን? የማንችል ከሆነ፥ ለምን?

5. ፍቅር በተግባር ካልተገለጸ ዋጋ የለውም። ፍቅርህን/ፍቅር ሽን ለመግለጽ የምታደርጋቸው/የምታደርጊያቸው ድርጊቶች ምንድናቸው?

"ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዳችሁ፥ እኔም የምወዳችሁ በመሆኔ በጣም እንደምናፍቃችሁ ምስክሬ እግዚአብሔር ነው።"

ፊልጵስዩስ 1፥8



የትምሕርቱ አዘጋጅ
መለሰ ወጉ

# ስንቅና ትጥቅ

በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።

**Ethiopian Outreach Ministry**
**P.O.Box 2241**
**York, PA 17405**
**U.S.A.**
**Phone/Fax: (717)846-2041**
**E-Mail: eomusa@aol.com**
**Internet Address:**
**www.ethiopianoutreach.com**

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድራሻ